# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም ዘወትር አርብ ከ7 p.m. ጀምሮ እየተገናኘን እንጸልያለን። ቃሉንም እንማራለን። በዚህ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ሁላችንም እንድንሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በተለያየ ጉዳይ እንዲጸለይላችሁ የምትሹም አገልጋዮችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ!

### የሕንጻ ፈንድ

የሕንጻ ፕሮግራማችን ላይ አሁንም ተሳትፎአችን እንዲቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። ስለዚህ አገልግሎት እየጸለይን አሁንም ጌታ እንደሚያሳስበን ለሕንጻ የሚሆን ስጦታን በመስጠት መትጋታችንን እንድንቀጥል በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን። ጌታ ይባርካችሁ!

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።" (2ጢ.ም. 1:7)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **May 20, 2018** | **ግንቦት 12፣ 2010 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ............. | ወንድም ሰለሞን ወመነ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

“ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ”

(መዝ. 1፡1)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመነ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ምስጉን ማን ነው? — ሁለት

ባለፈው ሳምንት እንዳየነው እግዚአብሔር ምስጉን የሚለው ሕዝብ በእርሱ የዳነውን ሕዝብ ነው። ስለዚህም ስለ ህዝቡ ሲናገር “እስራኤል ሆይ ምስጉን ነህ፤ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው?” (ዘዳ. 33፡29) ይለዋል። በእግዚአብሔር ማዳን ውስጥ የእርሱ ጥበቃና ቸርነትም እንዳለ አይተናል። ስለዚህ ማዳኑን የቀመሰ ምስጉን ሕዝብ ነው። ይህንን ሃሳብ ዛሬም ቀጥለን እናያለን።

መዝሙር አንድን ስናጠና እግዚአብሔር ምስጉን የሚለው ሰው ያለውን ባህርይ እንመለከታለን። መዝሙሩ “ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ” (ቁ. 1) በማለት ይጀመራል። በዚህ ቁጥር የተዘረዘሩት እግዚአብሔር ምስጉን የሚለው ሰው የማያደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ምስጉን አንደኛ በክፉዎች ምክር አይሄድም። ምክር አደገኛ ነገር ነው። ወይ ያፈርሳል ወይንም ይሰራል። በተለይ የክፉዎች ምክር ክፉ ነው። እንደ በልአም እና አኬጦፌል ያሉ ክፉ ምክርን የሚመክሩ አሉ። ምክራቸውን የተከተለ ወደ ክፋት ይሄዳል። ለዚህ ሃሳብ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሮብአም የተባለው የእስራኤል ንጉስ ነው። የእስራኤል ሽማግሌዎች የአባትህን ቀንበር አቅልልን በለው ንጉሱን ጠየቁት። እርሱም በዚህ ጉዳይ ላይ ምክር ጠየቀ። ሽማግሌዎች “ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን ብትገዛላቸውም፥ መልሰህም በገርነት ብትናገራቸው፥ በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል” (1ነግ. 12:7) በማለት መከሩት። እርሱ ግን የሽማግሌዎቹን ምክር ችላ ብሎ ከርሱ ጋር ያደጉትን ብላቴኖች ምክር ጠየቀ። እነርሱም “ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች... አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል፥ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ በላቸው” (ቁ. 10-11) ብለው መከሩት። ንጉሱም ብላቴኖቹ እንደመከሩት ለህዝቡ መለሰ። ህዝቡም ተከፍቶ “በዳዊት ዘንድ ምን ክፍል አለን? በእሴይም ልጅ ዘንድ ርስት የለንም” (ቁ. 16) ብለው ወደ ድንኳኖቻቸው ተመለሱ። ይሁዳም ለብቻው ተነጠለ። የተቀረው እስራኤልም በላያቸው ላይ ኢዮርብዓምን አነገሱ። ከዚህ ክፉ ምክር የተነሳ አገር ተከፈለ። ክፉ ምክር አይበጅም፤ ያፈርሳል። በክፉ ምክር ውስጥ የሚሰለጥነው የክፉ ሃሳብ ነው። ስለዚህ ምስጉን ሰው በክፉዎች ምክር አይሄድም። እንዲሁም ምስጉን ሰው በኃጢያተኞች መንገድ አይቆምም። ምስጉን ሰው ለሃጢያት የሚጋብዝን ሁኔታ ወደ ህይወቱ አያስገባም። አሁን የሃጢያተኞች መንገድ ሰፊ ነው። በኢንተርኔት የሚለቀቅ እርኩሰትን መለማመድ፣ ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ መሄድ፣ በማይገባን ስፍራ መገኘት በኃጢያት መንገድ መቆም ነው። ምስጉን ግን ይህንን አያደርግም። በሶስተኛ ደረጃ ምስጉን በዋዘኞች ወንበር አይቀመጥም። ዋዘኞች በእግዚአብሔር ነገር ይቀልዳሉ። መንፈሳዊውን እውነት ረብ እንደሌለው ይወስዳሉ። በጊዚያዊ ተድላና ጨዋታ ይወሰዳሉ። እግዚአብሔር ምስጉን የሚለው ሰው ግን እራሱን ከዚህ ይጠብቃል።

ወገኖቼ፡- እግዚአብሔር ምስጉን ይለናል። በልጁ ደም ቅድሶ አዲስ ህይወትን በመስጠት የተመሰጉኑና ክብር የሚገባቸው አድርጎናል። ነገር ግን ለዚህ ክብር የሚገባውን ህይወት መኖር ይጠበቅብናል። የክፉዎችን ምክር፣ የኃጢያተኞች መንገድና የዋዘኞችን ህበረት እናስወግድ። አሜን!